**መመሪያ ቁጥር 3/2012**

**የኮቪድ-19 ሥርጭትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈጸም የወጣውን ደንብ ለማስፈጸም በሚኒስትሮች ኮሚቴ የወጣ የግብይት ዘርፍ መመሪያ**

በመላ ሀገሪቱ በሚገኙ የተለያዩ ገበያ ቦታዎችና አገልግሎት ሰጪ የንግድ ተቋማት ከፍተኛ የሆነ የሕዝብ መጠጋጋት የሚስተዋል ሲሆን፣ ይህም ለኮቪድ 19 ወረርሽኝ ሥርጭት ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር በመሆኑ የቫይረሱን ሥርጭት፣ ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የግብይት ስርአቱን በተመለከተ የተለያዩ የጥንቃቄ እርምጃዎችን መውሰድ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የኮቪድ-19 ሥርጭትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈጸም የወጣውን ደንብ ለማስፈጸም በሚኒስትሮች ኮሚቴ የወጣው መመሪያ ቁጥር 2/2012 ላይ የግብይት ስርአቱን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ቢኖሩም አጠቃላይ በገበያ ቦታዎች እና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ጋር የሚኖረውን አካላዊ መጠጋጋትና መሰል ችግሮችን ለመፍታት በሚያስችል መልኩ በዝርዝር ያልተቀመጠ በመሆኑ ይህንን ክፍተት ለመድፈን የሚያስችል ዝርዝር ድንጋጌዎችን የያዘ መመሪያ ራሱን አስችሎ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የሚኒስትሮች ኮሚቴ የኮቪድ 19 ሥርጭትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 3/2012ን ለማስፈፀም በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 466/2012 አንቀጽ 7 መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ ‹‹ የኮቪድ-19 ሥርጭትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈጸም የወጣውን ደንብ ለማስፈጸም በሚኒስትሮች ኮሚቴ የወጣ የግብይት ዘርፍ መመሪያ ቁጥር 3/2012›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡



The Federal Democratic Republic of Ethiopia Federal Attorney General

Scanned by CamScanner

## 2. ትርጉም

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፣

1) "አዋጅ" ማለት የኮቪድ 19 ሥርጭትን ለመከላከል ፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የወጣው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 03/2012 ነው፣
2) "ደንብ" ማለት የኮቪድ 19 ሥርጭትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የወጣው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 03/2012 እና ማስፈጸሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 466/2012 ነው፣
3) **"ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር"** ማለት እንደቅደም ተከተሉ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፣
4) **"ባለድርሻ አካላት"** ማለት በዚህ መመሪያ ውስጥ ስማቸው የተጠቀሱ ወይም ይህን መመሪያ የሚያስፈጽሙ አካላት ናቸው፣
5) "የግብይት ቦታዎች" ማለትመሸጫ ሱቅን፣ ሚኒ ማርኬትን ፣ሱፐር ማርኬትን ፣ ሀይፐር ማርኬትን፣ ሞልን፣ አገልግሎት ሰጪ የንግድ ተቋምን እና ክፍት የገበያ ቦታን ያጠቃልላል፣
6) **"መሸጫ ሱቆች"** ማለት በመደብር ውስጥ በአንድ ወይም ከዚያ በላይ መስኮት በአንድ ወይም ከዚያ በላይ ሻጮች አማካኝነት በጅምላም ሆነ በችርቻሮ ንግድ የሚከናወንበት ቦታ ነው፤
7) **"ሚኒ ማርኬት ፣ሱፐር ማርኬት ወይም ሀይፐር ማርኬት"** ማለት ሸማቹ የሚገዛቸውን ዕቃዎች ዞሮ በማየትና በመምረጥ ግብይት የሚፈፅምበት ቦታ ነው፣
8) **"ሞል"** ማለት የተለያዩ የንግድ መደብሮች በአንድ ላይ አጠቃሎ የያዘ ሕንጻ ነው፣
9) **"ክፍት የገበያ ቦታዎች"** ማለት ከመደብር ውጭ ማንኛውም ግብይት የሚከናወንበት ቦታ ነው፣
10) **"አገልግሎት ሰጪ የንግድ ተቋማት"** ማለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ‹ሐ›፣ ‹መ› ፣ ‹ሠ› እና ‹ረ› ከተጠቀሱት ውጭ ያሉ የንግድ ሥራዎች የሚከናወኑበት ቦታን ያጠቃልላል፣

Scanned by CamScanner

11) **"የንጽሕና መጠበቂያ ቁሶች"** ማለት ኮቪስ 19ን ከእጅ ላይ ማስወገድ ወይም መከላከል የሚችል ደረቅ ወይም ፈሳሽ ሳሙና፣ የእጅ ጓንት፣ ሳኒታይዘር እና ሚቴን አልኮሆልን ያጠቃልላል፣

12) **"የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ"** ማለት ለዚሁ አላማ ተብሎ በፋብሪካ የተሰራ ማስክ፣ በቤት ውስጥ ከተለያዩ ጨርቃጨርቆች የተዘጋጀ ማስክ ወይም ማናቸውም አፍና አፍንጫን ለመሸፈን የሚያገለግል ልብስ ነው፣

13) በአዋጁና ደንቡ ትርጉም የተሰጣቸው ቃላትና ሐረጋት ለዚህ መመሪያም ያገለግላሉ፡፡

**3. የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በመላ ሀገሪቱ ግብይት የሚፈጸምባቸው ቦታዎች ላይ ሁሉ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## በግብይት ቦታዎች ላይ ሊወሰዱ ስለሚገባቸው የጥንቃቄ እርምጃዎች

**4. በመሸጫ ሱቆች ሊወሰዱ ስለሚገባቸው የጥንቃቄ እርምጃዎች**

በመሸጫ ሱቆች የሚከተሉት የጥንቃቄ እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው፡-

1) ማንኛውም በሱቆች ውስጥ ዕቃን የሚሸጥ ሰው በግብይት ወቅት አፍና አፍንጫውን መሸፈን አለበት፣

2) የሱቁ ባለቤት ወይም ማንኛውም በሱቁ ውስጥ የሚሸጥ ሰው በሸማቹና በሻጩ መካከል ሁለት የአዋቂ እርምጃ ርቀት ለመጠበቅ የሚያስችል መለያ ወይም መገደቢያ የማዘጋጀት ኃላፊነት አለበት፣

3) የሱቁ ባለቤት ወይም ማንኛውም በሱቁ ውስጥ የሚሸጥ ሰው በሸማቾች መካከል ሁለት የአዋቂ እርምጃ ርቀት ለመጠበቅ የሚያስችል መለያ ወይም መገደቢያ የማዘጋጀት ኃላፊነት አለበት፣

4) በሸማቾች መካከል ከሁለት የአዋቂ እርምጃ በታች አካላዊ መጠጋጋት እንዳይፈጠር ሻጩ እያንዳንዱን ሸማች በተናጠል የማስተናገድ ኃላፊነት አለበት፡፡

**5. በሚኒ ማርኬት ፣ሱፐር ማርኬት ወይም ሀይፐር ማርኬት ሊወሰዱ ስለሚገባቸው የጥንቃቄ እርምጃዎች፡-**

በሚኒ ማርኬት፣ ሱፐር ማርኬት ወይም ሀይፐር ማርኬት የሚከተሉት የጥንቃቄ እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው፡-

* በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ *
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Federal Attorney General

Scanned by CamScanner

1) ማንኛውም የሚኒ፣ የሱፐር ማርኬት ወይም የሀይፐር ማርኬት ባለቤት ወይም የሥራ መሪ በነዚህ ግብይት ቦታዎች መግቢያ በር ላይ ወደ ግብይት ቦታዎቹ የሚመጣ ሰው ንፅህናውን ለመጠበቅ የሚያስችሉትን ውሃና ሳሙና ወይም ሳኒታይዘር ማዘጋጀት አለበት፣

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚቀመጠው ሳሙና፣ ውሃ ወይም ሳኒታይዘር አካባቢን በማይበክል መንገድ መሆን ይኖርበታል፣

3) በነዚህ የግብይት ቦታዎች የሚሰሩ አስተናጋጆችና የሽያጭ ሠራተኞች የእጅ ጓንት እና የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ የማድረግ ግዴታ አለባቸው፣

4) በነዚህ የግብይት ቦታዎች ውስጥ ለሚደረጉ ግብይቶች ገንዘብ ተቀባይ እና ሽያጭ ሠራተኛ የተለያዩ መሆን አለባቸው፣

5) ወደእነዚህ የግብይት ቦታዎች የሚመጣ ማንኛውም ሰው በግብይት መግቢያ ላይ በተዘጋጀት የእጅ ንጽሕና መጠበቂያ ውሃና ሳሙና ሳይታጠብ ወይም በሳኒታይዘር እጁን ሳያጸዳ ማስገባት የተከለከለ ነው፣

6) ወደ ግብይት ቦታው የሚመጣ ማንኛውም ሰው የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ሳያደርግ ማስገባት የተከለከለ ነው፣

7) ማንኛውም የሚኒ፣ የሱፐር ማርኬት ወይም የሀይፐር ማርኬት ባለቤት ወይም የሥራ መሪ በሸማቾች እና በሠራተኞች መካከል ሁለት የአዋቂ እርምጃ ርቀት ለመጠበቅ የሚያስችል መለያ ወይም መገደቢያ የማዘጋጀት ኃላፊነት አለባቸው፣

8) ማንኛውም የሚኒ፣ የሱፐር ማርኬት ወይም የሀይፐር ማርኬት ባለቤት ወይም የሥራ መሪ ወይም የሽያጭ ሠራተኛ በሸማቾች መካከል ሁለት የአዋቂ እርምጃ ርቀት ለመጠበቅ የሚያስችል መለያ ወይም መገደቢያ የማዘጋጀት ኃላፊነት አለባቸው፣

9) ማንኛውም የሚኒ፣ የሱፐር ማርኬት ወይም የሀይፐር ማርኬት ባለቤት ወይም የሥራ መሪ በሠራተኞች መካከል ሁለት የአዋቂ እርምጃ ርቀት ለመጠበቅ የሚያስችል መጠበቂያ ወይም መገደቢያ የማዘጋጀት ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## 6. በሞሎች ሊወሰዱ ስለሚገባቸው የጥንቃቄ እርምጃዎች

በሞሎች የሚወሰዱ የጥንቃቄ እርምጃዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

1) የሞሉ ባለቤት በሞሉ በመግቢያ በር ላይ ወደ ሞሉ የሚመጣ ሰው ንፅህናውን ለመጠበቅ የሚያስችሉትን ውሃና ሳሙና ወይም ሳኒታይዘር ማዘጋጀት አለበት፣

Scanned by CamScanner

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ1 መሠረት የሚቀመጠው ሳሙና፣ ውሃ ወይም ሳኒታይዘር አካባቢን በማይበክል መንገድ መሆን ይኖርበታል፣

3) የሞሉ ባለቤት ወይም በሞሉ ውስጥ ሱቆችን ተከራይቶ የሚሰራ ወይም የሚያሰራ ሰው በሞሉ የሚሰሩ አስተናጋጆች የእጅ ጓንት እና የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ እንዲያደርጉ የማድረግ ግዴታ አለበት፣

4) የሞሉ ባለቤት ወይም በሞሉ ውስጥ ሱቀቆችን ተከራይቶ የሚሰራ ወይም የሚያሰራ ሰው ወደ ሞሉ ለመግባት የሚመጣ ማንኛውም ሰው መግቢያ በር ላይ በተዘጋጁት የእጅ ንጽሕና መጠበቂያ ውሃና ሳሙና ወይም ሳኒታይዘር እጅን ሳያጸዳ ማስገባት የተከለከለ ነው፣

5) የሞሉ ጥበቃዎች ወደ ሞሉ ለመግባት የሚመጣ ማንኛውም ሰው የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ሳያደርግ ማስገባት የተከለከለ ነው፣

6) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 እና 5 እንደየአግባቡ በሞል ውስጥ በሚገኙ ሚኒ ማርኬት፣ ሱፐር ማርኬት እና ሀይፐር ማርኬት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 7. በአገልግሎት ሰጪ የንግድ ተቋማት ሊወሰዱ ስለመገባቸው የጥንቃቄ እርምጃዎች

በአገልግሎት ሰጪ የንግድ ተቋማት የሚከተሉት የጥንቃቄ እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው፡-

1) የአገልግሎት ሰጪ የንግድ ተቋም ባለቤት ወይም ተቋሙን ተከራይቶ የሚሰራ ወይም የሚያሰራ ሰው መግቢያ በር ላይ ወደ ግብይት ቦታዎቹ የሚመጣ ሰው ንፅህናውን ለመጠበቅ የሚያስችሉትን ውሃና ሳሙና ወይም ሳኒታይዘር ማዘጋጀት አለበት፣

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚቀመጠው ሳሙና፣ ውሃ ወይም ሳኒታይዘር አካባቢን በማይበክል መንገድ መሆን ይኖርበታል፣

3) ወደ ንግድ ተቋማቱ የሚመጣ ማንኛውም ሰው መግቢያ ላይ በተዘጋጁት የእጅ ንጽሕና መጠበቂያ ውሃና ሳሙና ወይም ሳኒታይዘር እጅን ሳያጸዳ ማስገባት የተከለከለ ነው፣

4) ወደ ተቋማቱ የሚመጣ ማንኛውም ሰው የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ሰያደረግ ማስገባት የተከለከለ ነው፣

5) በተቋማቱ የሚሰሩ ሠራተኞች የእጅ ጓንት እና የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ማስክ የማድረግ ግዴታ አለባቸው፣

6) የአገልግሎት ሰጪ የንግድ ተቋም ባለቤት ወይም ተቋሙን ተከራይቶ የሚሰራ ወይም የሚያሰራ ሰው ከሰውነት ንክኪ የጸዱ የሆኑ ቴክኒካዊ መሳሪያዎች ማዘጋጀትና የመጠቀም ግዴታ አለበት፣

Scanned by CamScanner

7) ወደ ተቋሙ የሚገቡ ተገልጋዮችን የሰውነት ንክኪ ባለው ሁኔታ አካላዊ ፍተሻ ማድረግ የተከለከለ ነው፣

8) የአገልግሎት ሰጪ የንግድ ተቋም ባለቤት ወይም ተቋሙን ተከራይቶ የሚሰራ ወይም የሚያሰራ ሰው በተገልጋዮች እና በሠራተኞች መካከል ሁለት የአዋቂ እርምጃ ርቀት ለመጠበቅ የሚያስችል መለያ ወይም መገደቢያ የማዘጋጀት ኃላፊነት አለበት፣

9) የአገልግሎት ሰጪ የንግድ ተቋም ባለቤት ወይም ተቋሙን ተከራይቶ የሚሰራ ወይም የሚያሰራ ሰው በተገልጋዮች መካከል ሁለት የአዋቂ እርምጃ ርቀት ለመጠበቅ የሚያስችል መለያ ወይም መገደቢያ የማዘጋጀት ኃላፊነት አለበት፣

10) የአገልግሎት ሰጪ የንግድ ተቋም ባለቤት ወይም ተቋሙን ተከራይቶ የሚሰራ ወይም የሚያሰራ ሰው በሠራተኞች መካከል ሁለት የአዋቂ እርምጃ ርቀት ለመጠበቅ የሚያስችል መለያ ወይም መገደቢያ የማዘጋጀት ኃላፊነት አለበት፣

11) ሆቴሎች፣ ሬስቶራንቶች፣ ካፌዎች፣ ምግብ ቤቶች፣ የአትክልት ጭማቂ መሸጫ ቤቶች እና ተገልጋዮቻቸው የሚቀመጡባቸው ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎችና መሰል ቁሳቁሶችን ከእያንዳንዱ አገልግሎት በኋላ በአልኮል፣ በሲኒታይዘር ወይም የኮቪድ 19 ቫይረስን ሊያጸዳ በሚችል ማንኛውም ማጽጃ እንዲጸዳ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## 8. በክፍት የገበያ ቦታዎች ሊወሰዱ ስለሚገባቸው የጥንቃቄ እርምጃዎች

በክፍት የገበያ ቦታዎች የሚከተሉት የጥንቃቄ እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው፡-

1) በክፍት የገበያ ቦታዎች የሚሰራ የሸያጭ ባለሙያ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ የማድረግ ግዴታ አለበት፣

2) ሽያጩን የሚያከናውን ሰው ወይም ባለቤት በሸማችና በሻጭ መካከል ሁለት የአዋቂ እርምጃ ርቀት ለመጠበቅ የሚያስችል መለያ ወይም መገደቢያ የማዘጋጀት ኃላፊነት አለበት፣

3) ሽያጩን የሚያከናውን ሰው፣ ባለቤት ወይም የአካባቢው መስተዳደር በሸማቾች መካከል የአዋቂ ሁለት እርምጃ ርቀት ለመጠበቅ የሚያስችል መለያ ወይም መገደቢያ የማዘጋጀት ኃላፊነት አለበት፣

4) ሽያጩን የሚያከናውን ሰው፣ ባለቤት ወይም የአካባቢው መስተዳደር በሻጮች መካከል የአዋቂ ሁለት እርምጃ ርቀት ለመጠበቅ የሚያስችል መለያ ወይም መገደቢያ የማዘጋጀት ኃላፊነት አለበት፣

Scanned by CamScanner

5) በሸማቾች መካከል መቀራረብ እንዳይፈጠር ሻጭ እያንዳንዱን ሸማች በተናጠል የማስተናገድ ኃላፊነት አለበት፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለግብረ-ኃይል

**9. ስለግብረ- ሀይል**

1) በሚኒስቴሩ የሚመራ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሮች ኮሚቴ የሆነ የግብይት ጉዳዮች ግብረ-ኃይል ከዚህ በኋላ "ግብረ-ኃይል" እየተባለ የሚጠራ በዚህ መመሪያ ተቋቁሟል፤

2) ስለግብረ-ኃይሉ አባላት

ግብረ-ኃይሉ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ. የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተወካይ- - ሰብሳቢ፣

ለ. የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ተወካይ - - አባል፣

ሐ. የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ተወካይ - - አባል፣

መ. የጤና ሚኒስቴር ተወካይ - - አባል

ሠ. አንድ የተለየ ክልልን በሚመለከት ጉዳይ ላይ በየክልሎቹ የንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ሀላፊዎች ወይም አዲስ አበባ ወይም ድሬዳዋ ሲሆን የከተማው የንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ወይም አቻ ተቋማት ሀላፊዎች - - አባል፣

3) የግብረ-ኃይሉ ተግባርና ሀላፊነቶች፡-

ግብረ-ኃይሉ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች አሉት፤-

ሀ. በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ፣ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ እና በዚህ መመሪያ ውስጥ የተደነገጉትን ከግብይት ስርአት ጋር የተያያዙ ተግባራትን ይከታተላል፣ ያስፈፅማል፣

ለ. የዚህን መመሪያ አፈጻጸም በበላይነት ይከታተላል፣

ሐ. በየጊዜው አፈጻጸሙን ይገመግማል፣

መ./ ባለድርሻ አካላትን ያስተባብራል፣

ሠ. ለሚኒስትሮች ኮሚቴ ሪፖርት ያቀርባል፣

4) ግብረ-ኃይሉ የሚሰበሰብበትን ጊዜና አሰራሩን ራሱ በሚያወጣው እቅድ ይወስናል፣

5) የሚኒስትሮች ኮሚቴ እንደአስፈላጊነቱ የግብረ-ኃይሉን አባላት ቁጥር ወይም ስብጥር ሊቀይር ይችላል፡፡

የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ
The Federal ... Democratic Republic of Ethiopia Federal Attorney General

Scanned by CamScanner

### 10. የቴክኒክ ኮሚቴዎች

ግብረ-ኃይሉ የኮቪድ-19 ጋር ተያይዞ በገበያ ቦታዎች የሚኖረውን መጨናነቅ ሳቢያ ሊኖር የሚችለውን የቫይረሱን ሥርጭትን ለመከላከል፣ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የተለያዩ የቴክኒክ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፡፡

### 11. የክልል ግብረ-ኃይል

1/ ሁሉም ክልሎች ይህንን የአፈጻም መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል በየክልሎቹ ንግድን ለማስተዳደር ሥልጣን ባላቸው አካላት ወይም ቢሮዎች የሚመራ ግብረ-ኃይል የፌዴራሉን ግብረ-ኃይል አደረጃጀት ተከትሎ ያቋቁማሉ፣

2/ የክልል ግብረ-ኃይሎች ወቅቱን የጠበቀ የአፈጻጸም ሪፖርታቸውን ለፌደራል ግብረ-ኃይል ያቀርባሉ፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 12. የንጽሕና መጠበቂያ ቁሶች እንዲቀርቡ ስለማድረግ

ሚኒስቴሩ፡-

1) ኮቪድ 19ን ከእጅ ላይ ማስወገድ ወይም መከላከል የሚችሉ የንጽሕና መጠበቂያ ቁሶች በስፋት ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ እና በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ምቹ ሁኔታ የመፍጠር ኃላፊነት አለበት፣

2) መሠረታዊ የምግብ ሸቀጦች በስፋት ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ እና በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ምቹ ሁኔታ መፍጠር አለበት፣

3) የንጽሕና መጠበቂያ ቁሶች እና መሰረታዊ የምግብ ሸቀጦች ለኅብረተሰቡ በቀላሉ እና በተመጣጣኝ ዋጋ ተደራሽ ለማድረግ ምቹ ሁኔታ የመፍጠር ሀላፊነት አለበት፡፡

Scanned by CamScanner

13. **ተጨማሪ የገበያ ቦታዎች ስለማዘጋጀት፣**

ሁሉም ክልሎች በሥራ ላይ ያሉ የገበያ ቦታዎች በግብይት ወቅት በተገበያዮች መካከል የሚፈጠረውን ቅርርብ በመቀነስ የቫረሱን መተላለፍ ለመከላከል በሥራ ላይ ከሚገኙ የገበያ ቦታዎች በተጨማሪ ማኅበረሰቡ ከአካባቢ ሳይርቅ የሚገበያይባቸው ጊዜያዊና ቋሚ ሌሎች ጤናማና ምቹ የገበያ ቦታዎችን በበቂ ሁኔታ ማዘጋጀት አለባቸው፡፡

14. **አቅርቦትን በተመለከተ**

በየደረጃው የሚገኙ የሸማች ማኅበራት፣ የኅብረት ሥራ ድርጅቶች እና ሌሎች አደረጃጀቶች ለኅብረተሰቡ የሚያስፈልጉ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶችን በየአቅራቢያው በማቅረብ በተመጣጣኝ ዋጋ ለኅብረተሰቡ ያለአድሎ የማዳረስ ሥራ መስራት አለባቸው፡፡

15. **ገበያ ተብለው ከተከለሉ ቦታዎች ውጪ መገበያየት የተከለከለ ስለመሆኑ**

በሚመለከተው አካል ለገበያ ቦታነት ባልተከለሉ፣ ከሚታወቁና ከተፈቀዱ ገበያዎችና የግብይት ቦታዎች በስተቀር በመንገድ ዳር፣ በጎዳና ላይ ወይም በማንኛውም ቦታ ላይ መገበያየት የተከለከለ ነው፡፡

16. **የኤሌክትሮኒክስ ትራንዛክሽንን በተመለከተ**

1. ማንኛውም የኢንተርኔት ወይም ኦንላይን ግብይት የፈፀመ ድርጅት ወይም ነጋዴ ግብይት የተፈፀመትን ዕቃ ለገዥው በአድራሻው በመውሰድ የማስረከብ ግዴታ አለበት፣
2. የመንግሥት ተቋማት ደንበኞቻቸው በአካል ሳይገኙ በኤሌክትሮኒክ መንገድ አገልግሎት ማቅረብ እና ማግኘት የሚያስችሉ በመንግሥት /በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር/ የተዘጋጁ እና የተረጋገጡ ስርዓቶች የመጠቀም ግዴታ አለበት፡፡

17. **ሕጋዊ እና አስተዳደራዊ ተጠያቂነትን በተመለከተ**

1/ ይህን መመሪያ በመጣሱ የሚኖረው ተጠያቂነት በአዋጁ አንቀጽ 6 [illegible] ይሆናል፣

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Federal Attorney General

Scanned by CamScanner

2/ ይህን መመሪያ የጣሰ ማንኛውም ነጋዴ ሚኒስቴሩ ወይም ንግድን ለማስተዳደር በክልል ሥልጣን ያለው አካል የንግድ ፈቃዱን ያግዳል፡፡

**18. የተሻሩና ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች**

1. የመመሪያ ቁጥር 2/2012 አንቀፅ 22 ድንጋጌ በዚህ መመሪያ ተሽሯል፣
2. ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም አሰራር ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

**19. የመተባበር ግዴታ**

ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ሁሉም አካል የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**20. መመሪያው ተፈጻሚ ሚሆንበት ጊዜ**

ሀ/ ይህ መመሪያ በሚኒስትሮች ኮሚቴ ከጸደቀበት ዕለት ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፣

ለ/ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ተፈጻሚነት ዘመን ውስጥ ይህንን መመሪያ ለማሻሻል የሚያስፈልጉ ጉዳዮች ከተከሰቱ መመሪያው በሚኒስትሮች ኮሚቴ ሊሻሻል ይችላል፣

ሐ/ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ከተነሳ የዚህ መመሪያም ተፈጻሚነት አብሮ ያበቃል

**ሚያዝያ 30 ቀን 2012 ዓ/ም**

**የሚኒስትሮች ኮሚቴ**

Scanned by CamScanner